እውነተኛ ፍቅር

የተለያዩ ሰዎች ፍቅርን ልዩ ልዩ ትርጉም ይሰጡታል ። ለብዙዎች በተለይም በዚህ ዘመን የፍቅር ትርጉም በጾታ ልዩ የሆኑ ሰዎች በሚያደርጉት ግንኙነት የሚወሰን ነው ። በዚህ አመለካከት የፍቅር ጥልቅቱ ና ምጥቀቱ ፡ አበድኩልሽ ሞትሁልሽ ወይም አበድሁልህ ሞትሁልህ እስከ ግብረ ፡ሥጋ ድረስ ነው ። እንዲህም ሲባል ሁሉም ሴጋ ብቻ አይደለም ማለት አይደለም ፤ ብዙ ጋኑ ሲታዩ ነው እንጂ ። ፍቅርን በዚህ አመ ለካከት ተተብለው ፡ ርምጃ ጀምረው ፡ ይሆ ነኝ ትሆንኝ ተባብለው ሲጋብቻ በትተው የቤተሰብ ድንጉርጉር በሳምንቱ ፡ በውሩ ኋላም ቢል በዓመቱ ያልደረሰባቸው በጣ ም እነስተኞች ናቸው ። ምክንያቱም ፍቅሩ በመልክ ማለትም በውበቱ በውበቷ ላይ ብቻ የተመሠረተ ስለሚሆን ነው ። አብዛ ኛውን ጊዜ ይህ ዓይነቱ ፍቅር ከእግዚአብ ሔር እምልክ የራቁ ፡ በከሀደት ባሕር የተ ጠመቁ ወይም የአምልኮት መልክ ኖሯ ቸው ከእግዚአብሔር ይልቅ ተድላን የሚ ወዱ ሰዎች የተለማመዱት ፡ የሚለማመ ዱት ነው ።

በቤተሰብደረጃ የሚታይ ፍቅርም አሰ ። እና ት ዘመኔ መር እርግዛ አምጣ የመለደችውን (ጾትን) የሥጋዋን ቁራጭ ልጅዋን ትወደ ዋለች (ታለች) ። ባሏም የኑር ጓደኛዋ ፡ የት ዝር ተካፋይ ፡ በሥጋ ደረጃ ከእናት ከአባቷ ይልቅ በቅርብ የምታገኘው አጋዥዋ በመ ሆኑ በእርሱ ትምክህት አላት ። በእንዲሁም አባት ልጁንና ሚስቱን ይወዳል ። በቤተሰቡ ውስጥ ባለመግባባት ፡ ባለመስማማም ምክን ያት ከሚነሣው አምባጓሮ በስተቀር እርስ በርስ መተሳሰብ ፡ መዋደድ አብዛኛውን ጊዜ ይታያል ፡ ይህ ዓይነቱ መዋደድ (መፋ ቀር) ሰማያዊት መንግሥትን በሚጠባበቅ በክርስቶስ እግዝያንና ምንም እንኳ በእግዚ አብሔር እምነት ባይኖራቸው በሞራል በላ በሩ ቤተሰቦች ሁሉ ይታያል ። በኑሮዋቸው መጣማም የሌላቸው ባልና ሚስት ሁል ጊዜ ከመነታረክና በትር ከመማዘዝ ብሎም ከመፋታት በስተቀር ፍቅር ላይኖራቸው ይችላል ።

ሰው ሁሉ ባልንጀራውን (በማብሩ የሚ መሰለውን) ይወዳል ። ፍቅሩ ግን ዘላቂነት ያለው ሊሆንም ላይሆንም ይችላል ።

እውነተኛ ፍቅር ክርስቶስን ያስተምማል ፡ ምክንያቱም ሐዋርያው ዮሐንስ በመጀ መሪያው መልእክቱ " ... እግዚአብሔር ፍቅር ነውና ።" 4 ፡ 8 ብሎ እንደጸፈ የፍ ቅርን መሠረት ራሱን ፍቅርን (እግ ዚአብሔርን) በቅድሚያ ማወቅና መረዳት ስለሚያስፈልግ ነው ። እግዚአብሔርን የሚያውቅ በፍጹም ልቡ ፡ በፍጹም ነፍሱ የሚያመልክ ሰው የሥጋውን ምኞት የሚ ቆጣጠር ፡ በእጨብራቂዋ ዓለም ከመጉም ጀት ራሱን የሚገታ መሆን ይገባዋል ። በዚህም ለነገር ሁሉ ታጋሽ ይሆናል ። ብዙ ት በቀላሉ በሚታለሉበት በከንፈር ወዳ ጅነት ማለትም ሥር-አልባ በሆነ የሥጋን ሥምሮት ለማርካት በሚደረገው "ፍቅር" አይነደፍም ። ከዚህ ይልቅ ከሁሉም የሚበል ጠውን የእግዚአብሔርን ትእዛዝ ሁሉ ያክ ብራል ። በዚህ አባባል እውነተኛው ፍቅር ከዓለማውያን "ፍቅር" የተለየ ነው ። በእውነትም ነው ። ሐዋርያው ዮሐንስ ስለእውነተኛው ፍቅር ጽፏል ። "በእርሱ በኩልበሕይወት እንኖር ዘንድ እግዚአብ ሔር አንድ ልጁን ወደ ዓለም ልኮታልና ። ፍቅርም እንደዚህ ነው ፡ እግዚአብሔር እርሱ ራሱ እንደወደደን ስለኃጢአታችንም ማስተስሪያ ይሆን ዘንድ ልጁን እንደ ላከ እንጂ እኛ እግዚአብሔርን እንደወደድ ነው አይደለም ።" 1ዮሐ.4 ፡ 10 ሲል ፍቅ ር ራስን ለወዳጆቹ ቀርቶ በደልን ለፈጸሙ በት እንኳ አሳልፎ እስከመስጠት የጠለቀ ነው ። ሕያው ክርስቶስን ስንበድለውና ስና ሳዝነው በማሳዘናችንና በመበደላችን ኋላ የሚደርስብንን መራር ሐዘን ተመልክቶ ቅንጣት በደል ሳይኖርበት ስለእኛ ሥጋን ለብሶ በምድር ላይ ተመላለሰ ፡ እስከሞት ወደናል ። ፍቅር ይህ ነው ። ይህ ፍቅር አምላክ እርስ በራሳችን እንድንዋደድ ተናግ ሯል ። ስለዚህም ትእዛዙን ልንከተል ይገ ባናል ። እግዚአብሔርን የሚወድ ከእርሱ ተወልዷል ፡ እግዚአብሔርንም ያውቃል ። እግዚአብሔርን ወደድሁ ለማለት በመጀ መሪያ ደረጃ የምናየውን ወንድማችንን ስናፈቅር እንደሆነ በታላቁ መጽሐፍ ፡ በ መጽሐፍ ቅዱስ ተጽፎ እናገኛለን ። የእርስ በእርስ መዋደድ ሳይኖር እግዚአብሔርን እወዳለሁ ማለት ግን እውነትነት የሌለው አፍአዊ ፡ እንዲያውስ ለይስሙላ የተባለ "ፍቅር" ነው ።

ፍቅርን (እውነተኛውን) መከታተል ለ እምነታችን ክርስቲያን ተገቢ ነው ። ከእምነት ና ከተስፋ ብልጫ ያለው ፍቅር ነው ። ጠላት ዲያብሎስ በእግዚአብሔር ሰዎች መካከል እየገባ መታቀርን ሊያመጣ ይወዳል ። እር ሱ ምንገዜም አያርፍምና ፡ ሰሞኖች ፡- "እግዚአብሔርን እመን ፡ እርሱንም ውደድ ጠላትህን ግን ጥላ" እያለ ይመክራል ። በዚ ህም የተሰናከሉ አማንያን ቁጥር በቀላል የሚገመት አይደለም ። እነርሱም ከእውነተ ኛ ፍቅር የራቁ እልመሰላቸውም ። ፍቅር ግን ይታገሣል ። (1ቆሮ. 13 ፡ 4)

እንድ አባት ስለክርስቶስ ሲመሰክሩ የፍቅርንም ጠቃሚነት ተናግረው ነበር ። ትምህረታቸውም "ፍቅር የሌለው ሃይማ ኖት አያጸድቅም" ብለዋል ። ተላቅ ፡ ክፉ ት ፡ ተንኮል በሞሉበት ልብ እነዚህ የክ ፉት ሥራዎች ተጠርገው እስካልወጡ ድረ ስ ለፍቅር ቦታ እንደማይሰጡ እሙን ነው ። ክርስቲያን ማን በአምላኩ ኃይል እነዚህን ደምስሶ ፍቅርን በመተካት እምነትንና መ ልካም ሥራን አዋሕዶ በመጽናት ጽድቅን ለማግኘት እንዲተጋ ይገባዋል ።

በአጠቃላይ አነጋገር ምንም እንኳ በተለ ያዩ ሰዎች ስለፍቅር የተለያዩ ትርጉሞችና አመለ ካከት ቢሰጠውም እውነተኛው ፍቅር ራሱን ስለሰው ልጆች አሳልፎ የሰጠው ሕያው ክር ስቶስ ነው ። እርሱን ልናፈቅር ይገባናል ። እ ርሱ በእኛ መካከል እንዳለ የምናውቅ እርስ በርሳችን ስንዋደድ ነው ። ክርስቲያኖች ሆይ በእውነተኛው ፍቅር እንመላለስ ። በ ስም "ፍቅር" ብለን የሥጋ ፈቃዳችንን በመ ፈጸም እንዳንጐዳ ማስተዋል ይኖርብናል ። 1ቆሮ. 13 ፡ 1 ። መጨረሻና የመጀመሪያው የሐዋርያው የዮሐንስ መልእክት ብናነብ ስለፍቅር በበለጠ ለመማር እንችላለን ።

ወቢቶ ይማዋው